በስደት ላይ ያለው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት

THE LEGITIMATE HOLY SYNOD OF THE
ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH
PUBLIC RELATIOIN OFFICE IN EXILE

ቀን: ግንቦ7 15/2010
Date: May 23/18
ቁጥር: ግንቦ7 001
Ref. No: MAY 001

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐ3:16

# በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የሚመራው ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የመምህር እንደሥራቸው አግማሴ መኮንን ያለፍትህ ለ24 ዓመታት መታሰራቸውን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ።

## «ይባዕ ቅድሜከ ገዓሮሙ ለሙቁኃን=የእስረኞች ጩኸታቸው ወደፊትህ ይግባ። (መዝ.78፥11)

በአገራችን ያልፍትህ የታሰሩ ብዙ ኢትዮጵያን በየጨለማ ቤቱ ተዘግተው በመከራ ላይ መገኘታቸውን ከተጣሉበት ከጥልቅ ምድር ስር ሆነው በመጮኽ ላይ ይገኛሉ። የጊዜና የዘመናት ባለቤት ቅዱስ እግዚአብሔር የወሰነው ጊዜ እስከሚደርስ ፤ ሰውን ሰው ሊያጠፋው ይደክማል እንጅ ያለፈጠረውን ሰው፤ሰው ማጥፋት አይችልም።

ሰዎችን ለማጥፋት የሚደረገው ክፋት የሰዎችን ክፋታቸው ከመግለጽ ያለፈ ትርጉም እንደሌለው የመምህር እንደሥራቸው ሕይዎት ይመሰክራል።

ሙቷል ብለን ተስፋ ከቆረጥንበት 24 ዓመታት በኋላ በሕይዎት መኖሩን የሰማንበት ጭላንጭል ትልቅ ምስክር ነውና።ያሰሯቸውም ቢሆኑ ለመግደል እንደወሰዷቸው ያውቃሉ ። ዱካቸውን አጥፍተው የወሰዱበትን ሳይናገሩ ዘመናት አልፈዋልና። የቤተክርስቲያን አምላክን የምናደንቀው ከሞት በኋላ ስለአለው ሕይወት ብቻ ሳይሆን በየቀኑ ከገደዳዮቻችን እጅ ጠብቆ ማቆየቱንም ጭምር ነው።

መምህር እንደሥራቸው በሕይዎት መቆየት የእግዚአብሔር ቸርነት መገለጫ እንጅ አፋኞቹ ከገደሉት ቆይተዋል። ጥፋት እንኳን ቢኖረው በህግ ፍርድ ቤት አቅርቦ ማስፈርድና ማሰር ሲቻል ያለምንም ጠያቂ 24 ዓመታት በጨለማ እሥር ቤት ማቆየት ሰብአዊ ርህራሄ የጎደለው አሳፋሪ ተግባር ነው። ይህን እኩይ ድርጊት በጽኑዕ እያወገዝን አሁንም ሳይውል ሳያድር ይፈታ ዘንድ ጥሪ እናቀርባለን።

ጠቅላይ ሚኒስተሩ የሚያደርጓቸውን በጎ ምግባራት እያደነቅን በሱዳንና በኬንያ ብሎም በሳውዲ አረቢያ ያሉ እስረኞችን ለማስፈታት ያደርጉትን እንቅስቃሴ ብናመሰግንም። በእራሳችን የመሬት ጉድጓድ ውስጥ/ግራውንድ ፕሪዝን ውስጥ / ያለፍርድ እየተሰቃዩ ያሉ ወገኖችን ቅድሚያ መስጠት የፍትህ ፈላጊነት አንዱ መገለጫ ነው ብለን እናምናለን። መምህር እንደሥራቸው አግማሴ መኮንን ከሌሎች በዘርፉ ካሉ ባለሞያዎች በላይ የተለየ ሀብተ ዕውቀት የተሰጣቸው የተክሌ አቋቋምና የድጓ መምህርነትን በሚያስደንቅ ችሎታ ከነሙሉ ጥበቡና አስተምህሮቱ የያዙ አይነተኛ ሊቅ ናቸው።ይህን የዘመናችንን ያሬድ



80 TYCOS DRIVE TORONTO ONTARIO M6B 1V9 CANADA
ethiopianorthodoxchurchtoronto@gmail.com Tel. # 416-781-4802 fax # 416-781-0220

በሰሜን ዋሻዎች ውስጥ  በድንገት ሲሰወር ጥልቅ በሆነ ሀዘንና ትካዜ ውስጥ ተውጠን ቆይተናል።እኛም  በግፍ መሰደዳችን ፍለጋውን በአገር እርቀት ምክንያት ሁኔታውን በቅርብ ለመከታተል ባንችልም  በሁኔታው እንድናዘንና እንድንተከዝ አድርጎን ነበር።

አሁን ግን ሁሉንም ማድረግ የሚችለው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር የተስፋ ጭላጭል ሰጥቶናል። በመሆኑም በለውጥ ጎዳና ያሉት ጠቅላይ ሚኒስቴርም አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣሉ ብለን ተስፋ ብናደርግም እውን ሁኖ እስከምናየው  ድረስ ስለዚህ የቤተክርስቲያን ሊቅና እንደሱ ያለፍርድ ስለታሰሩት በተደጋጋሚ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ተረድተናል።

መላው የፍትሕ ፈላጊ ኢትዮጵያውን ሆይ ! ይህን ታላቅ ሊቅ ለማስፈታት / አካልን ነጻ የማውጣት  እንቅስቃሴ  በቻላችሁት  መጠን  እንድታደርጉ  ጥሪ  እያቀረብን  ጠቅላይ ሚኒስተሩም ይህን ታላቅ የቤተክርስቲያን ሊቅ ለቤተክርስቲያኗ ክብር ሲባል ከምንም በፊት እንዲፈታ እንዲያድርጉና በጨለማ እስር ቤት ውስጥ ያሉ ወገኖች ሁሉ በሕግና በሕግ ብቻ ጉዳያቸው እንዲታይ እንዲያደርጉና የጨለማውን እስር ቤት  የሚመሩ አካላት በግልጽ በሕግ እንዲጠየቁ እንዲሆን እያሳሰብን። አሁንም እየቀጠለ ያለውን በሶማሌ፣ በኦሮሚያ በቤንሻጉል ጉሙዝ በጋምቤላ እየተካሄደ ያለው ሰዎችን ከሚኖሩበት ቦታ የዚህ ዘር አባላት ናችሁ በማለት የማፈናቀልና የመግደል ተግባር በአስቸኳይ እንዲቆምና ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፈለገውና በመረጠው ሥፍራ የአካባቢውን ደንብና ሕግ ተከትሎ በሰላም ሰርቶ የመኖር መብቱ ተከብሮ እንዲኖር ሕግና ፍትሕ የሰፈነባት አገር እንድትሆን መንግሥት የሕዝቦቹን ሰብአዊ መብቶች አክብሮና አስከብሮ እንዲሰራ እያሳሰብን።

የቆየውን የኢትዮጵያዊነት የመተዛዘን ስሜትንና የሰው መብቶችን የጣሱ ግለሰቦች ሕግ ፊት ቀርበው ተገቢውን ቅጣት አግኝተው ሀገሪቱ በሕግ የምትዳደር መሆኗን የማሳየት ግዴታ አለበዎት ብለን እናምናለን። ይህን ግዴታ ለመወጣት ቁርጠኝነቱ የሚጀመረው መምህር እንደሥራቸውንና እንደርሳቸው አለአግባብ የታሰሩትን  ከእስር ተፈተው ከቤተሰባቸው ጋር ሲገናኙ  እንደሆነ በማመን በአስቸኳ እንዲፈቱ የኢትዮጵያን መንግሥት አጥብቀን እንጠይቃለን።

እግዚአብሔር ሕዝቧንና ሀገራችን ኢትዮጵያን ይባርክ።

ሊቀ ኅሩያን ምሣሌ እንግዳ
በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ
ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ
Rev.F.L.K. MESSALE ENGEDA
Administrator of Ethiopian Orthodox
Tewahedo Church in Canada